EthioLion.Com

# "ጥሩ ኢትዮጵያዊነት" የጊዜው ቁልፍ ጥያቄ

ተጻፈ በፍቅር ግንቦት 2001 ዓ·ም· አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ethio.fikir@yahoo.com

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

## "ጥሩ ኢትዮጵያዊነት" የጊዜው ቁልፍ ጥያቄ

በዚህ ጽሁፍ ጥሩ በሚለው ገላጭ ቃል መጠቀም የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያት የምናከብረውንና የምንወደውን በብዙ መስዋትነት የቆየንን የማንነታችንን መገለጫ በቀና መንፈስ ለመግለጽ ያመች ዘንድ ነው። ይህችን አጭር ጽሁፍ ለመጻፍ በዋና ምንጭነት እንዲሁም መነሻ ምክንያትነት ያገለገለኝ በ1986 ዓም በፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም የተጻፈው ***ኢትዮጵያ ከየት ወደየት*** የሚለው መጽሃፍ ነው።

ኢትዮጵያዊ የሚለው ስም ኢትዮጵያ በምትባለው ሃገር ክልል ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ሁሉ የጋራ መጠሪያ ማንነት መግለጫ ስም ነው። ይህን ማንነት መካድና ማሰካድ ከዚያም አልፎ ከተተኪው ትውልድ ህሊና ውስጥ ሸርሽሮ ለማጥፋት መስራት እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም አገላለጽ ራስንና ዘርማንዘርን በመካድ መነሻ መሰረትን የሚያሳጣ በሽታ ነው።

ስለዚህ በተለይም ጥሩ ኢትዮጵያዊነት የብዙ የተለያዩ ህብረተሰቦች የመከባበርና የመፈቃቀድ፣ የአስተዋይነትና የሚዛናዊነት እንዲሁም የጨዋነት ባህርይ መገለጫ ማንነት ነው። ይህም ማንነት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚስማማ አላማ ያለው ብዙዎች በሰቃይና በመከራ፣ በብዙ ጭቆናና ጥቃት አልፈው ያገኙት ኩራትና ክብር እንዲሁም አትንኩኝ ባይነት ጭምር ነው።

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ዋነኛ ትኩረቱ ኢትዮጵያዊነትን ባማሩ ቃላት መግልጽን አይደለም። ይህን ስራም እንደ ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ ያሉ ብዙ ጥሩ ኢትዮጵያዊያን ልባቸው በኢትዮጵያዊነት ፍቅር እየቃተቱ የዘመሩላትንና የተቀኙላትን ኢትዮጵያዊያን ድርሻ በአክብሮት እያሰበ ለዚህ ጽሁፍ ወዳነሳሳው ዋና አላማ ይጓዛል።

ጥሩ ኢትዮጵያዊነት በምን መልክ ይገለጻል? ይህ ጥሩ ኢትዮጵያዊነትስ በዘመናችን እምን ደረጃ ላይ ይገአኛል? ለተተኪው ትውልድስ እንዴት ይተላለፋል? የሚሉትን ጥያቄዎች በመዳሰስ ኢትዮጵያ በዘመናችን ኢትዮጵያዊነትን የሚያከብር ለኢትዮጵያውያን የወገነ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥቅም የበላይነት የሚሰራ እና በኢትዮጵያውያን የታመነ ስርአትና መንግስት የመመስረትን አስፈላዝጊነት በተመለከተ ሃሳብ ለመሰንዘርና ይልቁንም ውድ አንባቢያን በዚህ ቁምነገር ዙሪያ ሃሳብ እንዲለዋወጡ መነሻ ለመሆን በዚህም መልኩ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ በተሻለ መልኩ የጋራ አስተሳሰብ (common understanding) እንዲኖረን የበኩሌን ለማድረግ ነው።

created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ኢትዮጵያዊነት እንደሌሎች የአለም አገራት ዜጐች መገለጫ ሁሉ ኢትዮጵያውያን መገለጫ መለያ ስም ነው።ታዲያ ጥሩ ኢትዮጵያዊነትም ከጥሩ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እንደምንማረው የእምነት የአብሮ ተከባብሮና ተፋቅሮ የመኖር ስር የሰደደ ማህበራዊ ኑሮ መገለጫ ነው።

በአንፃሩ ግን ይህ ጥሩ ኢትዮጵያዊነት ከጊዜ ወደጊዜ ችግር እየገጠመው መምጣቱን እናያለን። የዚህ ችግር ምንጭ ደግሞ የኢትዮጵያ አስተዳደር የፈጠረው ችግር እንጂ ሃገሪቱ ኢትዮጵያ አይደለችም።

ከተለያዩ ያደጉ ሃገራት ዜጎች ዜግነት መገለጫ እንደምንማረው የእድገታቸው መገለጫ መሰረት በተለያየ ቀለም ዘር ሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች ጎጥ ይዞ በመናቆር ሳይሆን እነዚህን ልዩነትነቶች ያከበረ ጠንካራና ግልጽ አንድነት የመመስረታቸው ምስጢር ነው። ይህም አንድነታቸው በጋራ የመስራታቸው የመኖራቸው ብሎም  የእድገታቸው መገለጫ የዜግነት ምጠሪያ የማንነት ስማቸውንም በኩራት በፍቅርና በክብር የመጠቀማቸው ምስጢር ነው።

ስለዚህ እኛም ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን የዚህችን ሃገር ህዝቦች ሰላምና ብልጽግና እንዲሁም የህዝቦቿን አንድነት የማይሹ ገዢዎች በፈጠሩብን የስነልቦና ተጽእኖ ከአንድ የተለየ ህብረተሰብ ቋንቋ ወይንም ሃይማኖት ጋር ብቻ የተቀራኘ አድርገን በጥርጣሬ የምናይበትን የመለያየት ስሜት መተው ይገባናል። በዚህች ሃገራችን ውስጥ ያለን የብዙ ቋንቋዎች ሃይማኖቶች የረጅም ዘመን የግጭትና የመተባበር የጸብና የፍቅር ነገር ግን ያለመለያት ተጋብቶ ተዋልዶና ተዛምዶ የመኖር የመተሳሰር ማንነት ነው። ይህ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን እንዲያድግ እንዲጎለብት እንጂ እንዳይናጋ በተናጋ ቁጥር ደግሞ ለዚህች ታላቅ ሃገር ህዝቦች ከፍተኛ ጉዳትና ውድቀት መምጣት ምክንያት መሆኑ እንደማይቀር በመረዳት አስፈላጊውን ትኩረት ሁሉ ማድረግ ይገባናል።

ኢትዮጵያዊ ማንነት ለብዙ ዘመናት የነበረና ያለ ወደፊትም ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚኖር መሆኑ የታወቀ ነው። ይልቁንም ይህ ማንነት ስርአት ባለው መልኩ ለተተኪው ትውልድ የመተላለፉ ጉዳይ ችግር ውስጥ የወደቀና የሁሉንም ጥሩ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። አዲሱ ትውልድ በተለይም አሁን ባለንበት የወያኔ ስርአት በተለያየ መልኩ ይህንን ማንነት ክደው በሚያስክዱ የሃገር መሪዎች የስነልቦና ጦርነት ውስጥ ተዘፍቅ ይገኛል። ይህ አደገኛ ተተኪ የሚያሳጣ ጦርነት እጅግ ስር ሳይሰድ ከወዲሁ ሃይ ካልተባለ በኢዮጵያችን  እንዴት ማንነቱን አክብሮ ለራሱና ለሃገሩ ህዝብ ጥቅም የሚቆም ትውልድን ማፍራት ትችል ይሆን?

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional





EthioLion.Com

የማህበራዊ ሳይንስ ጠበብት እንደሚነግሩን የህብረተሰብ መሰረት የሆነው እያንዳንዱ ቤተሰብ ይህን የማንነት ጥያቄ በአትኩሮት ሊያጤነውና የቀጣዩን ትውልድ የራሳቸውን ማንነት ክደው ከሚያስክዱት የጊዜያችን ገዢዎች መጠነሰፊ ዘመቻ ልጆቹን በጥሩ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ በማሳደግ ሊታደግ ይገባል። ይህም ቤተሰብ ላይ ያተኮረ ትውልድ የማዳን መፍትሄ በተለይ ኢትዮጵያዊ ወገንተኛ መንግስታዊ ስርአት እስከሚመሰረት አይነተኛ መፍትሄ ነው።

የወያኔ ስርአት ኢትዮጵያን ለተለያየ አደጋ አጋልጦ የሰጣት ይህን ማንነት ችግር ውስጥ ለመጣል ባለው አደገኛ እቅድ መሰረት ነው። ይህንን አባባል በተጨባጭ ለመረዳት ሩቅ መሄድም ሆነ ብዙ ማንበብ የሚሻ ጉዳይ አይደለም። ለዚህም የወያኔ ባለስልጣናትን ባላመኑበት የኢትዮጵያዊነት ማንነት ኢትዮጵያን የማስተዳደር ስራ ውስጥ ገብተው የያዙትን ሃገርና ትውልድን የማጥፋት ዘመቻ መመልከት ብቻ በቂ ነው። በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይም እንደተገለጸው የኢትዮጵያዊነት ችግር ኢትዮጵያ ያለመሆኗንና ችግሩ የሃገሪቱ አስተዳደር ችግርም መሆኑን ከዚሁ በቀላሉ መረዳት አዳጋች አይደለም።

የወያኔ አስተዳደር ገና ስልጣን ላይ እንደተቆናጠጠ ከጅምሩ በኢትዮጵያውያን ልዩነት ላይ በማትኮር አንዱን ዘር በሌላው ላይ የማነሳሳት መንገድን የመረጠና ለዚህም አላማ ማስፈጸሚያነት የተነደፈ የሃገር አከላለል፣ የትምህርት፣ የበጀት ምደባና ሌሎችንም የሃገር አስተዳደር ስርአቶች መዘርጋቱን ልብ ይሏል። ኢትዮጵያዊ ማንነቱን የካደ እንዴት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን እንደማይወግን ደግሞ ይኸው የወያኔ ስርአት በግልጽ በተደጋጋሚ ያኢትዮጵያን ድነበር ቆርሶ በመስጠትና ሃገሪቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ከጎረቤት ሃገራት ጋር የመኖር መርሆ መከተል ከዚያም አልፎ ሃገሪቱን በማይጠቅም የውክልና ጦርነት ውስጥ በመዝፈቅ ቀላል የማይባል የሰላም ማጣት ስጋትን መፍጥሩን መመልከቱ ጥሩ መገለጫው ሆኖ እናያለን።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በዚህ የወያኔ ስርአት የተደቀነብንን የማንነት ችግሮች ለመፍታት ደግሞ ይህ በምርጫ የተሸነፈ ስርአት ባጠመደልን የመለያያ ወጥመድ ሳንጠመድ በተባበረ አኢትዮጵያዊ ክንድ ጊዜው የጠየቀውን አማራጭ ሁሉ በመጠቀም መጣልና በምትኩም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተሞላበት ፍጹም ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ኢተዮጵያዊ ማነነቱን ያልካደ ለኢትዮጵያውያን ጥቅምና ብልጽግና በፍጹም ቅናት የሚሰራ የአኢትዮጵያውያን ፍቅርና ድጋፍ ያለው አዲስ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ስርአት ለመገንባት ሁላችንም የበኩላችንን በማድረግ የጊዜውን የጥሩ ኢትዮጵያዊነት ጥሪ መመለስ ይገባናል።

EthioLion.Com

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

አዲስ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ስርአትን የመገንባት ጥሪ ለመመለስ ደግም በተለይም በዚህ ወያኔ ውድቀቱን አይቀሬነት ተመልክቶ በሚጠራሞዝበት በአሁኑ ወቅት ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ይህንንም ታላቅ ሃገራዊ ጉዳይ በትገቢው ጊዜና ጥንቃቄ መከወን ኢትዮጵያዊነትን በስደት በድህነት እንዲሁም በተረጂነት መታውቅ የሚያበቃበትን አዲስ ስርአት ግንባታ በጥሩ መሰረት ላይ የማቆም ወደር የማይገኝለት የጥሩ ኢትዮጵያዊ የዜግነት ቁልፍ ተግባር ነው።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ የተባበረ ክንድ ወደተሻለ ስርአት ታመራ ዘንድ የአምላክ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!**

EthioLion.Com



created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional